# በኢሳፕ2 የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ትግበራ ግኝቶች

## *የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ምንድን ነው?*

መንግስት ለህብረተሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚውያውለውን ገንዘብ ከተለያዩ ክፍያዎች፣ ከግብር፣ ከተለያዩ ምንጮች ከሚያገኛቸው ድጋፎች ያሰባስባል፡፡ የተሰባሰበው ኃብት ከህብረተሰቡ ጋር ቀጥታ በሚገናኙ አገልግሎት ሰጪዎች በኩል አልፎ፣ ሳይሰረቅና ሳይባክን በመጨረሻ ለተጠቃሚዎች መድረስ አለበት፡፡ የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት የተመደበው በጀት በታሰበበት አግባብ ሥራ ላይ መዋሉን፡- ጥራት ያለው አገልግሎት ለዜጎች፣ በተለይ ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ወገኖች መሰጠቱን ያጠናል፡፡ በኢሳፕ2 የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት በብሔራዊና በክልል ደረጃ ለወረዳ ስለተመደበው በጀት መጠን፣ ፈሰስ የተደረገው መጠንና አለቃቀቁ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ መዘግየቶችን ተረድቶ ማወቅ ላይ ይወሰናል፡፡

የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ሙያዊ ልምምድ ሲሆን ሁሉም የማሕበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚዎች ይህን ልምምድ በድርጅቶቻው ውስጥ ለማካሄድ የሚያስችል የኦዲትና ጥናት አቅም የሏቸውም፡፡ የማሕበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚዎች ማነቆዎችን ከለዩ በኋላ አንዳንድ አሰራሮች ላይ ማሻሻያ ለማድረግ በፊት ለፊት ውይይት ወቅት ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ ከሁሉ በላይ ጠቃሚ የሆነው ነገር በዚህ ልምምድ ትግበራ ወቅት የዜጎችን አቅም መገንባት በመቻሉ በጀቱን በትኩረት መከታተልና የበለጠ ግልጸኝነት እንዲሰፍን መጠየቅ ችለዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ አገልግሎት ሰጪዎች ወደፊት ለሥራ የሚመደበውን ኃብት ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል፡፡

## *የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት - 8 ደረጃዎች*

1. **የኃብት ፍሰት መስመሩን ካርታ መስራት፡- -** ይህ ደረጃ የገንዘብ ድጋፎችን ግብዐቶች የሚጓዙበትን መስመር ማግኘትና እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጡና በጀቱን ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎች ያሏቸውን ሚናና ኃላፊነቶች ሚታወቅበት ነው፡፡
2. **የሂደቱን ዓላማ፣ ስፋትና ተግባሪ አካላትንመለየት፡-** በዚህ ደረጃ ባለድርሻ አካላት ምን ማወቅ እንደሚፈልጉና ለምን እንደሚፈልጉ ስምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡
3. **መጠየቆችን ማዘጋጀት፡-** መጠይቆች የሚዘጋጁት ለጥያቄዎቻቸው እውነተኛ ምላሾችን ማግኘት እንዲችሉ ነው፡፡ በምላሹ የተገኘው መረጃ ኃቀኛ ለመሆኑ በተለያዩ ምንጮች መረጋገጥ አለበት፣ ይህ ማለት አንዱ ጥያቄ ለተለያዩ አካላት ቀርቦ ምላሾቻቸውን ማግኘት ማለት ነው፡፡
4. **ናሙና መውሰድና የመስክ ሙከራ -** የመጠይቆቹ ብዛትና የቃለ መጠይቁ ብዛት በበርካታ ነገሮች የሚወሰን ቢሆንም፣ በአፍሪካ በሚታወቁ የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ውስጥ 25 በመቶ የሚሆኑት አገልግሎት መስጫዎች ይካተታሉ፡፡ ናሙናው ውስጥ ያለመካተት ችግሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ መጠይቆቹን በመስክ መሞከር እጅግ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይህም የናሙና መረጃ ሰብሳቢዎችን ከሥራቸው ባህርይ ጋር ያስተዋውቃቸዋል፣ ለጥናቱ ጥቅም ላይ የሚውሉ መሳሪያዎችም ላይ ማሻሻያዎች ለማድረግ ያስችላል፡፡
5. **ጥናቱን ማካሄድ፡-** በዘፈቀደ የተመረጡ ሥፍራዎችን መመልከት፣ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ድንገት መጎብኘት፣ እንዲሁም መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች ደጋግሞ ማመሳከር ለጥናቱ ጠቃሚ እርምጃዎች ናቸው፡፡
6. **የመረጃ ትንተና፡-** የጥናቱን ዓላማና የመጠይቁን አቀራረጽ መሰረት በማድረግ ዜጎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉት አቀራረብ መልኩ መረጃዎች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡
7. **የፊት ለፊት ውይይትና መረጃ ማሰራጨት፡-** የጥናቱ ግኝቶች በዜጎችና በአገልግሎት ሰጪዎች መካከል ውይይት እንዲደረግ የሚያስችሉ፣ ግልጸኝነት፣ ተጠያቂነት፣ ብሎም ለአገልግሎት መሻሻል መንገድ የሚከፍቱ መሆን አለባቸው፡፡ ኃላፊዎች ዜጎች የሚያቀርቧቸውን እሮሮዎች እንዲሰሙ እድል ያገኛሉ፣ ምላሾቻቸውና የተደረሱባቸው ስምምነቶች በማጠቃለያ ሪፖርት ላይ ተካትቶ በጋራ የተነደፈውን የድርጊት መርሀ-ግብር እንዲያግዝ በስፋት ይሰራጫል፡፡
8. **ክትትልና ተቋማዊ መልክ ማስያዝ፡-** የየአካባቢው የመንግስት አካላት የመንግስት ወጪዎችን መከታተያ ጥናት ጥቅም ላይ አውለው ከሆነ ዜጎች ለዚሁ ተብሎ ያዋቀሯቸውን ኮሚቴዎችና ሥብሰባዎች በመጠቀም ክትትል ማድረጋቸውን ቢቀጥሉ ተመራጭ ነው፡፡ የመንግስት የውስጥ ክትትልና ገለልተኛ በሆኑ አካላት የሚደረጉ ኦዲቶች ወጪዎች ለታቀደላቸው ተግባር መዋላቸውን ለማረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

## *የሲቪል ማበረሰብ ተቋማት የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናትን ለቀጣይ ጥቅም ላይ ሲያውሉ፡-*

- **ትኩረት፡-** የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናትን ጥቅም ላይ ለማዋል ዜጎች በገንዘብ አወጣጥና በቁሳቁሶች ወይም በአገልግሎት ጥራት ላይ ጥያቄ ሲኖራቸው ቢሆን ይመረጣል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ያልተወሳሰበና ሊመረመር የሚፈለገው ነገር ግልፅ መሆን አለበት ፡፡
- **ቀለል ያለ አሰራር መጠቀም፡-** የተመረጠው የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ታሳቢ ያደረገው የአገልግሎት መስጫ ተቋሙ፣ ቀበሌው ወይም ወረዳው ተጠያቂ የሚሆንበትን ያልተማከለውን የገንዘብ አመዳደብ ሥርዐት መሆንና አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ የወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች ወይም የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ኮሚቴን ማሳተፍ፡፡ የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናትን መተግበር ለዜጎች ከበድ ስለሚል የማሕበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮች ከየአካባቢው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ዜጎችን ከማሳተፋቸው በፊት የኃብት ፍሰት ካርታ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ***ፖሊሲዎችን ማወቅ፡-*** ለምሳሌ ወረዳው ለትምህርት ቤቶች በጀት የሚያከፋፍለው የትምህርት ቤቶችን የውስጥ ገቢ አቅም ተንተርሶ ቢሆን፤ ክልሎች እንደየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ አገር አቀፍ ፖሊሲዎችን የማስተካከል እድል እንዳላቸው መረዳት፡፡
- **የወጪ ሰነዶችን ማረጋገጥ፡- የመጋዘን የገንዘብ ሰነዶችን እንዲያሳዩአቸው** ለወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ጥያቄ ማቅረብ፡፡ የተገዙ ቁሳቁሶች በመጋዘን ውስጥ መኖራቸውንና ለግዢዎች የተሰበሰቡ ደረሰኞችን አለፍ አለፍ እያሉ መመልከት፡፡ የሥራ ውሎችንና የጨረታ ሰነዶችን መመርመርና የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ወይም የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የበጀቱ መረጃ ለዜጎች በሚያመች መልኩ ማጠቃለያ እንዲሰሩ መጠየቅ፡፡
- **ጥረቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ፡-** አንድ የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ማካሄድ ብቻውን በመንግስት ገንዘብ አወጣጥ ሂደት ላይ ለውጥ ለማምጣት በቂ አይሆንም፡፡ ትምህርት የሚቀስሙበትንና አቅማቸውን የሚያጎለብቱበት ልምድ ስለሚሰጣቸው የሴክተሩን የተለያዩ መዋቅሮች፣ የማሕበረሰቡን የአስተዳደር ኮሚቴዎችና የአገልግሎት መስጫ ቦርዶችን በመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ትግበራ ሂደት ውስጥ ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ተሳትፎ የመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናትን አቅም በማጎልበት የገንዘብ አወጣጥ ልምድንና ሂደትን ከጊዜ ወደ ጊዜ ያሻሽለዋል፡፡

## *በመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት ውስጥ ለቀጣይ የዜጎች ተሳትፎ፡-*

- **የማሕበረሰብ ተሳትፎ የገንዘብ፣** የጉልበትና የቁሳቁስ መዋጮ ከማድረግ ያለፈ ነው፡፡ መንግስት የሕብረተሰብ ተሳትፎ መዋቅሮች በየደረጃው ቢኖሩትም እነዚህ ቦታዎች በዜጎች የመንግስት መዋቅር አካል ተደርገው ስለተወሰዱ ሰዎች ሲሾሙ ውጤታማ እንቅስቃሴ እንደማያደርጉ በመንግስት ወጪዎች መከታተያ ጥናት አማካኝነት ታውቋል፡፡ በኢሳፕ2 ለችግር ተጋላጭ ወገኖችና ማሕበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ካደረጓቸው እንቅስቃሴዎች፤ ለማሕበረሰቡ የተለያዩ ኃሳቦች ከነበሯቸው እውነተኛ ውክልናና ለፕሮጀክቶች ግንባታ እውን መሆን ካደረጓቸው ድጋፎች ብዙ ትምህርት መውሰድ ይቻላል፡፡
- **የማሕበረሰብ መዋጮ፡-** የየአካባቢው የመንግስት አካላት ማሕበረሰቡ ለፕሮጀክቶች ግንባታ ለሚያደረጓቸው አብዛኛው ጊዜ ትርጉም ያላቸው የገንዘብ መዋጮዎች ተገቢውን ተጠያቂነት ቢያሳዩ ከዜጎች ተገቢውን አመኔታ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
- **የቁሳቁሶች ጥራት፡-** አገልግሎት ሰጪዎችም ሆኑ ተቀባዮች የዕቃዎች ግዢ በቀረበው ጥያቄ መሰረት እንደማይከናወንና እንደሚዘገይ ተመልክተዋል፡፡ ይህን ችግር በከፊል የግዢ ጥያቄዎች ባለው በጀት ማዕቀፍ ውስጥ ካለመቅረባቸው ጋር አያይዞ መግለጽ ይቻላል፡፡
- **የበጀት ግልጸኝነት፡-** የወረዳው በጀት በሁሉም ወረዳዎች በግልጽ ቦታ ቢለጠፍም የካፒታል በጀቱ የት ሥፍራ እንደሆነና ለምን ተግባር እንደሚውል ለይቶ ስላማያሳይ ዜጎች ለዚህ ብዙም ፍላጎት አያሳዩም፡፡ ለዜጎች በቀበሌ ደረጃ የሚደረጉ ግንባታዎችና ለተለየ የፕሮጀክት ሥራ የተመደበ ገንዘብን መከታተል የበለጠ ውጤታማ ነው፡፡ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የፕሮጀክት ኮንትራት ውሎችን ማጠቃለያ መስራት፤ የዘርፉ መስሪያ ቤቶች ደግሞ ለግንባታው በጀት የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡
- **በክልልና ባልተማከለ በጀት አሰራር የሚመጡ ገንዘቦች፡-** ወረዳዎች በክልሉ አማካኝነት የሚመደበውንና ለፕሮግም የሚመደቡትን በጀቶች ለይተው ማወቅ አለባቸው፡፡ ወረዳው ተጠያቂ ከሚሆንባቸው ገንዘቦች መካከል ብሎክ ግራንት በጀት፤ በአካባቢው የሚሰበሰቡ ግብሮችና የማሕበረሰብ መዋጮዎች ይገኙባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ ለዜጎች አቅጣጫ ማሳየት መንግስት ለሚያደርጋቸው ወጪዎች ተጠያቂ ማድረግ እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡